# የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ኃይሎች ኅብረት (ኢዴኃኅ)
# UNITED ETHIOPIAN DEMOCRATIC FORCES (UEDF)

## ከኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ኃይሎች ኅብረት (ኢዴኃኅ) የተሰጠ መግለጫ

### በአኝዋክ ሕዝብ ላይ ያነጣጠረው ጭፍጨፋ ይቁም፣
### አስጨፍጫፊዎችና ጨፍጫፊዎች ለፍርድ ይቅረቡ!

በጋምቤላ የአኝዋክ ወገኖቻችን ላይ ቅዳሜ ከታህሳስ 3 ቀን 1996 ዓ.ም ጀምሮ የተፈፀመውን የግፍ ጭፍጨፋና በተባበሩት መንግስታት የስደተኞች ኮሚሽን ሠራተኞች ላይ የደረሰውን ግድያ የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ኃይሎች ኅብረት አጥብቆ ያወግዛል፡፡

ሕወሓት/ኢሕአዴግ የመንግስት ሥልጣን ከያዘ ጀምሮ እንደዚህ ዓይነቱን የግፍ ጭፍጨፋ በሰላማዊ ሕዝብ ላይ በቀጥታ ሲያካሂድና እንዲካሄድም ሲያደርግ አዲስ አይደለም፡፡ ኢ-ዴሞክራሲያዊ አገዛዙን በሚቃወሙትና ለመሰረታዊ ሰብዓዊ መብታቸው የቆሙ ወገኖች ላይ ተመሳሳይ እርምጃ በል ልዩ የአገሪቱ ዜጎች ላይ ወስዷል፡፡ ለአብነት ያህልም በሸኮ-መዥንገር ሕዝብ ላይ በቴፒና በሲዳማ ሕዝባ ላይ በአዋሳ ከተማ ላይ ያካሄዳቸው ጭፍጨፋዎች የቅርብ ጊዜ ትውስታዎች ናቸው፡፡

የሕዝብ አንድነት የሚያባንነው ይህ አገዛዝ አናሳ ልዩነቶችን በማጋነንና አዳዲስ አለመግባባቶችን ሆን ብሎ በመፍጠር በመቻቻልና በመከባበር ለዝንታለም አብረው በኖሩ ብሔር/ብሔረሰቦችና የኅብረተሰብ ክፍሎች መካከል ጠብና አምባጓሮ የሚያነሳሳ ፖሊሲ በማራመድ የብዙ ንፁሃን ዜጎች ደም በከንቱ እንዲፈስ አድርጓል፤ ቤት ንብረትም አውድሟል፡፡

አሁንም በጋምቤላ የተደረገው ይኸው ነው፡፡ ከዚህ ቀደም በኑዌር ብሔረሰቦች መካከል ልዩነት እንዲፈጠርና የንፁሐን ደም እንዲፈስ አንዱ ለሌላው ጠላት እንደሆነና ለደም መፋሰሱ ተጠያቂ ሌላው እንደሆነ በተለመደው መሰሪያዊ የከፋፍለህ ግዛው ብቻ ሳይሆን የከፋፍለህ አጥፋው ዘይቤ ልዩነቶችን በማራገብ ላይ እንደነበር የሚታወቅ ነው፡፡

ታኅሣሥ 3 ቀን 96 ዓ.ም ጀምሮ በአኝዋክ ብሔረሰብ ላይ በማነጣጠር ለደረሰው የግፍ ጭፍጨፋ አገዛዙ የሰጠው ምክንያት በአንድ በኩል ሦስት የመንግስት ሰራተኞች ከሌሎች የተመድ የስደተኞች ኮሚሽን ሰራተኞች ጋር አኝዋኮች በሚኖሩበት አካባቢ በመገደላቸውና ለግድያውም አንዋኮችን ተጠያቂ አድርጎ በማቅረብና ገዳዮች ላይ

ዋና መስሪያ ቤት (Main Office)
ፖ.ሳ.ቁ. 18733 አዲስ አበባ ÷ ኢትዮጵያ
P.O.Box 18573 Addis Ababa, Ethiopia
ስልክ ቁጥር (Tel.No) 251-1530945 ፋክስ (Fax)

ሰሜን አሜሪካ (North America)
P.O.Box 73246
Washington DC 20056-3246, U.S.A
(Tel.No) 202-291-4217 (Fax) 202-291-7645

የተወሰደ እርምጃ እንደሆነ፤ በሌላ ጊዜ ደግሞ አኝዋኮች በኑዌሮች ላይ የወሰዱት የርስ በርስ ግጭት እንደሆነና ለዚሁም ተጠያቂ አኝዋኮች እንደሆኑ፣ ይኸው በኑዌሮች ላይ እንደተነጣጠረ በማስመሰል ለማምታታት ሞክሯል።

የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ኃይሎች ኅብረት በማንኛውም ኢትዮጵያዊ ወገናችን ላይ የሚደርስ ማንኛውንም ዓይነት ፀረ-ሕዝብ እርምጃ አጥብቆ ይኮንናል። በዜጎች መካከል መግባባትና ሰላም ሰፍኖ ኢትዮጵያዊያን ተከባብረውና ተቻችለው እንዲኖሩ ለጋራ ብልጽግና በጋራ እንዲሰሩ ማስቻል የኅብረቱ የወደፊት ራዕይ ሲሆን ለተሻለ ሥርዓት ከሚያደርገው የትግል ዓላማ አንዱ ነው።

በአኝዋክ ሕዝብ ላይ በማነጣጠር ለተፈፀመው ግፍ ወንጀሉን የፈፀሙት የመንግስት አካላት፣ ባለስልጣኖችና ግለሰቦች ለፍርድ ባስቸኳይ እንዲቀርቡ ኅብረቱ አጥብቆ ይጠይቃል። አንድ ሕዝብን ለይቶ የማጥቃት ዘረኛ እርምጃን አስቁሞ፤ በጋምቤላ ክልል ኗሪዎች መካከል ያለው ውጥረት እንዲረግብና ሰላም እንዲሰፍን አስፈላጊውን ሕጋዊ እርምጃ በመውሰድ ሁኔታውን ማረጋጋት ከአገዛዙ ይጠበቃል። እንዲሁም ለተጐዱ ወገኖች አስፈላጊ እርዳታ የሚደርስበትን ሁሉ በአፋጣኝ ማከናወን ያለበትን መንግስታዊ ሃላፊነት እንዲወጣ እናሳስባለን።

ሀገራዊና ዓለም-አቀፋዊ እርዳታ ሰጭዎች በቦታው በመገኘት በቀጥታና በቅርብ ሁነው የተጐዱትን ወገኖች እንዲረዱ፤ የሰብዓዊ መብት ተሟጋቾችና የነፃው ፕሬስ አባላት ሁኔታውን እንዲዘግቡ እቀባ እንዳይደረግባቸው እንጠይቃለን።

አገዛዙም ሕዝብን እርስ በርስ ለማናቆር የሚከተላቸውን የተንኮል እርምጃዎች በአስቸኳይ እንዲያቆም አጥብቀን ስናሳስብ ተጠያቂነት እንዳበትም ለማስገንዘብ እንወዳለን።

**በአኝዋክ ሕዝብ ላይ ጥቃት የፈፀሙ ወንጀለኞች ለፍርድ ይቅረቡ!**
**የኢትዮጵያ ሕዝብ ተቻችሎ በአንድነት መኖር በዘረኞች ሴራ አይደፈርስም!!**

*የኢትዮጵያ ሕዝቦች ዴሞክራሲያዊ ኃይሎች ኅብረት (ኢዴኃኅ)*
*ታሕሳስ 13 ቀን 1996 ዓ.ም*
*አዲስ አበባ*